# አማራጭ የሀይል አገልግሎት አቅራቢ ከመምረጥዎ በፊት ሊጠይቋቸው የሚገቡ ጠቃሚ ጥያቄዎች

# (Important Questions to Ask Before Selecting an Alternative Utility Service Provider)

ከአማራጭ የሀይል አገልግሎት አቅራቢ ጋር የሚገቡት ውል ከተለመዱትና ከትትል ከሚደረግባቸው የአገልግሎት አቅራቢዎች በተለየ መልኩ የሚደረግ የግል ስምምነት በመሆኑ የተወሰኑት ለተጠቃሚዎች ጥበቃ የሚያደርጉ ደንቦች ተፈፃሚነት ላይኖራቸው የሚችል መሆኑን ልብ ማለት ጠቃሚ ነው።

**ከአማራጭ የሀይል አገልግሎት አቅራቢ ጋር ለመስማማት ሳስብ ዓላማዬ ምንድን ነው?** ወጭ ለመቆጠብ? ለአካባቢ ብክለት መቀነስ አስተዋፅኦ ለማድረግ? የታዳሽ ሀይል አማራጭ ተጠቃሚ ለመሆን? በአገልግሎት ሰጭው የቀረበ ልዩ ጥቅም ለማግኘት? ከአማራጭ የሀይል አገልግሎት አቅራቢ ጋር ለመስማማት ያሰቡባቸውን ምክንያቶች ለይተው ቢያወጡ ትክክለኛውን ውሳኔ ለመወሰን ይረዳዎታል።

**አማራጭ የሀይል አገልግሎት አቅራቢው በዲ.ሲ. አገልግሎት እንዲሰጥ ፈቃድ አግኝቷል?** አገልግሎቱን ለመስጠት ፍላጎቱን የገለፀልዎት ድርጅት በኮሎምቢያ ግዛት የንግድ ስራ ለመስራት ከፐብሊክ ሰርቪስ ኮሚሽን ፈቃድ የተሰጠው መሆኑን ይጠይቁ። ፈቃድ የተሰጣቸው አገልግሎት ሰጭዎችን ዝርዝር ከፐብሊክ ሰርቪስ ኮሚሽን ድረ-ገፅ dcpsc.org መመልከት ይችላሉ።

**ለአገልግሎቱ መክፈል ያለብዎት የክፍያ ተመን ምን ያህል ነው?** ዓላማዎ ወጪ መቀነስ ወይም የተለየ አገልግሎት ማግኘት ሊሆን ይችላል። ነገር ግን፣ ስለ ክፍያ ተመኑ እርግጠኛ መሆን እንዳለብዎት አይዘንጉ። እስከ ስምምነቱ ማብቂያ ጊዜ ድረስ በአገልግሎት ክፍያ ተመኑ ላይ ለውጥ እንደማይኖር የአገልግሎት ሰጭው የፅሁፍ ማረጋገጫ መስጠት ይችላል?

**አሁን የሀይል አገልግሎት የሚያገኙበትን የክፍያ ተመን እና የአማራጭ ሀይል አቅርቦቱን ተመን ለማነፃፀር እገዛ ያገኛሉ?** የሚቀርቡት የአገልግሎት ሰጪ ዝርዝር ክፍያዎችና ታክሶች አሰደንጋጭ ሊሆኑ ይችላሉ። አብዛኞቹ የአገልግሎት ተጠቃሚዎች የክፍያዎችን ዝርዝር በማቅረብ የሚያግዛቸው የገለልተኛ ሦስተኛ ወገን እርዳታ ያስፈልጋቸዋል። ኦፊስ ኦፍ ፒፑፐልስ ካውንስል (ኦ.ፒ.ሲ)በዚህ ጉዳይ ላይ ሊረዳዎት ይችላል። እንደ ምሳሌ የሚያገለግል የአገልግሎት ክፍያ ንፅፅር ከድረ-ገፅ www.opc-dc.gov ማግኘት ይችላሉ።

**አገልግሎት ሰጭው አገልግሎቱን ለመስጠት እንደ ቅድመ-ሁኔታ የሚፈልጋቸው የግል መረጃዎች ምን ምን ሊሆኑ ይችላሉ?**
የውል ስምምነቱ ከመደረጉ በፊት፣ በምንም አይነት ሁኔታ፣ የሶሻል ቁጥር፣ የባንክ አካውንት ቁጥር፣ የመንጃ ፈቃድ ወይም ክሬዲት ካርድ እንዲሰጡ መገደድ የለብዎትም። እነዚህን ነገሮች በቅድሚያ የሚጠየቁ ከሆነ፣ ከፈተኛ ጥንቃቄ ያደረጉ ዘንድ ኦ.ፒ.ሲ ይመከርዎታል።የባንክ አካውንት ወይም ክሬዲት ካርድ መጠቀም፣ እርስዎ ክፍያዎን በሚመችዎ መንገድ ለመፈፀም የሚጠቀሙበት አማራጭ እንጂ የግድ አስፈላጊ መሆን የለበትም። በተጨማሪም፣ ከአገልግሎት ሰጭው የክሬዲት ሪፖርት ለማግኘት መጠየቅና ሪፖርቱን ማግኘት የሚችሉ መሆኑን ማወቅ ይገባወታል።

**የአገልግሎቱ ተጠቃሚ እንዲሆኑ ተገቢ ያልሆነ ግፊት እንዳለ ይሰማዎታል?**
ማንኛውም ህጋዊ የሆነ አገልግሎት፣ ግፊት በተሞላበት መልኩ በሚደረግ የሽያጭ ዘዴ ላይ የተመሰረተ መሆን የለበትም። የአገልግሎቱ ተጠቃሚ ለመሆን ከመወሰንዎ ወይም በስልክ ከመስማማትዎ በፊት፣ዝርዝር ክፍያዎችንና ሊኖሩ የሚችሉ ቅጣቶችን ያካተተውን ሙሉ የስምምነቱ ግልባጭ ማግኘት እንዲችሉና እንዲያዩት መጠየቅ የሚገባዎ መሆኑን ኦ.ፒ.ሲ ያስገነዝባል።

**የእኔ የግል መረጃ በምስጢር ይያዛል?**
በተጨማሪም፣ ድርጅቱ የእርስዎን የግል መረጃ በምስጢር የሚይዝ ወይም የደንበኞቹን ዝርዝር መረጃ ለሌሎች መረጃውን ለሚፈልጉ አካላት (ለምሳሌ የግብይት ጥያቄ መልዕክት ላኪዎች) የመሸጥ መብት ያለው መሆኑን ማረጋገጥ እንደሚገባ ኦ.ፒ.ሲ ያሳውቃል።

**ምንም እንኳ ወደ አማራጭ የሀይል አገልግሎት ሰጭ ቢቀይሩ፣ ነባሩ የሀይል ስርጭት አገልግሎት ድርጅት አማራጭ ሀይሉን ከቤትዎ የማድረሱን አገልግሎት የሚቀጥል መሆኑን ያውቃሉ?** አብዛኛውን ጊዜ፣ የትኛውንም የሀይል አቅራቢ ቢመርጡ፣ አገልግሎቱን ለማግኘት ለአካባቢው የሀይል ስርጭት አገልግሎት ሰጭ ድርጅት (local utility)ደንበኛ መሆን ይኖርብዎታል። በመሆኑም፣ ክፍያው እንዴት እንደሚሆን፣ የክፍያው ቢል መቼ እንደሚደርስዎና መቼ መክፈል እንዳለብዎ ቀደም ብለው ማወቅ ይኖርብዎታል። ለሁለቱም ኩባንያዎች ተገቢውን ክፍያ በሰዓቱ መክፈልዎን የማረጋገጡ ሀላፊነት የእርስዎ ነው።

**የአንድን አዲስ የሀይል አቅራቢ ድርጅት የአገልግሎት ስምምነት ማቋረጥ በተመለከተ ምን አይነት ደንቦች አሉ?**
በመጨረሻም፣ አገለግገሎቱን እንደጀመሩ በሚቀጥሉት ትቂት ሳምንታት ውስጥ ወይም ከዚያም በኋላ በሚኖረው የአገልግሎት ስምምነት ወቅት፣ በማንኛውም ምክንያት፣ ስምምነቱን የማቋረጥ አማራጭ ያለዎት መሆኑን በጥንቃቄ እንዲያጤኑ ኦ.ፒ.ሲ ይመክራል። ከመፈረምዎ ወይም ስምምነቱን ቢቃል ከመቀበልዎ በፊት፣የሙከራ ጊዜ መኖሩንና የስምምነቱ ወቅት ከመጠናቀቁ በፊት አገልግሎቱ ቢቋረጥ ቅጣቱ ምን እንደሚሆን መጠየቅ ያስፈልጋል።

**የደንበኛ አገልግሎታቸው ምን ያህል አመርቂ ነው?** የአገልግሎት ሰጭዎችን በመምረጡ ሂደት፣ የአገልግሎት አሰጣጥ ጥራት ሌላው ወሳኝ መመዘኛ ነው። አገልግሎት ሰጭው በአካባቢው ለማህበረሰቡ ክፍት የሆነ ቢሮና የደንበኞቹን ጥያቄ የሚቀበልበት የአካባቢ ስልክ መስመር ያለው መሆኑን ማረጋገጥ ጠቃሚ ነው።

ተጨማሪ መረጃ ለማገኘት ከፈለጉ፣ የኦፊስ ኦፍ ፒዩፐልስ ካውንስልን ስልክ ቁጥር 202-727-3071፣ ኢሜይል አድራሻ ccceo@opc-dc.gov፣ ወይም ድረ-ገፅ www.opc-dc.gov መጠቀም ይችላሉ።

በኮሎምቢያ ግዛት የማህበረሰብ ካውንስል ቢሮ
1133 15th Street, NW, Suite 500 | Washington, DC 20005
ስልክ: 202.727.3071 | ፋክስ: 202.727.1014 | TTY/TDD: 202.727.2876